# እንኳን በደህና መጡ

## ለ Washington Apple Health

ቁጥጥር የሚደረግበት እንክብካቤ እቅድ ውጪ የሆነ ሽፋን



Washington State Health Care Authority

[English] Language assistance services, including interpreters and translation of printed materials, are available free of charge. Call 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Amharic] የቋንቋ እገዛ አገልግሎት፣ አስተርጓሚ እና የሰነዶችን ትርጉም ጨምሮ በነጻ ይገኛል፡፡ 1-800-562-3022 (TRS: 711) ይደውሉ፡፡

[Arabic] خدمات المساعدة في اللغات، بما في ذلك المترجمين الفوريين وترجمة المواد المطبوعة، متوفرة مجاناً، اتصل على رقم 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Burmese] ဘာသာပြန်ဆိုသူများနှင့် ထုတ်ပြန်ထားသည့် စာရွက်စာတမ်းများဘာသာပြန်ခြင်းအပါအဝင် ဘာသာစကားအထောက်အကူဝန်ဆောင်မှုများကို အခမဲ့ရနိုင်ပါသည်။ 1-800-562-3022 (TRS: 711) ကိုဖုန်းခေါ်ဆိုပါ။

[Cambodian] សេវាជំនួយភាសា រួមមានទាំងអ្នកបកប្រែផ្ទាល់មាត់ និងការបកប្រែឯកសារបោះពុម្ព គឺអាចរកបានដោយឥតគិតថ្លៃ។ ហៅទូរស័ព្ទទៅលេខ 1-800-562-3022 (TRS: 711)។

[Chinese] 免费提供语言协助服务，包括口译员和印制资料翻译。请致电 1-800-562-3022 (TRS: 711)。

[Korean] 통역 서비스와 인쇄 자료 번역을 포함한 언어 지원 서비스를 무료로 이용하실 수 있습니다. 1-800-562-3022 (TRS: 711)번으로 전화하십시오.

[Laotian] ການບໍລິການດ້ານພາສາ, ລວມທັງນາຍແປພາສາ ແລະ ການແປເອກະສານຕີພິມ, ມີໄວ້ໃຫ້ຟຣີໂດຍບໍ່ຄິດຄ່າ. ໂທຫາເລກ 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Oromo] Tajajilli gargaarsa afaanii, nama afaan hiikuu fi ragaalee maxxanfaman hiikuun, kaffaltii malee ni argattu. 1-800-562-3022 (TRS: 711) irratti bilbilaa.

[Persian] خدمات کمک زبانی، از جمله مترجم شفاهی و ترجمه اسناد و مدارک (مطالب) چاپی، بصورت رایگان ارائه خواهد شد.با شماره 1-800-562-3022 (TRS: 711) تماس بگیرید.

[Punjabi] ਭਾਸ਼ਾ ਸਹਾਇਤਾ ਸੇਵਾਵਾਂ—ਦੁਭਾਸ਼ੀਏ ਅਤੇ ਪ੍ਰਿੰਟ ਕੀਤੀ ਹੋਈ ਸਮੱਗਰੀ ਦੇ ਅੰਨੁਵਾਦ ਸਮੇਤ—ਮੁਫ਼ਤ ਉਪਲੱਬਧ ਹਨ। 1-800-562-3022 (TRS: 711) 'ਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ।

[Romanian] Serviciile de asistență lingvistică, inclusiv cele de interpretariat și de traducere a materialelor imprimate, sunt disponibile gratuit. Apelați 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Russian] Языковая поддержка, в том числе услуги переводчиков и перевод печатных материалов, доступна бесплатно. Позвоните по номеру 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Somali] Adeego caawimaad luuqada ah, ay ku jirto turjubaano afka ah iyo turjumid lagu sameeyo waraaqaha la daabaco, ayaa lagu helayaa lacag la'aan. Wac 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Spanish] Hay servicios de asistencia con idiomas, incluyendo intérpretes y traducción de materiales impresos, disponibles sin costo. Llame al 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Swahili] Huduma za msaada wa lugha, ikiwa ni pamoja na wakalimani na tafsiri ya nyaraka zilizochapishwa, zinapatikana bure bila ya malipo. Piga 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Tagalog] Mga serbisyong tulong sa wika, kabilang ang mga tagapagsalin at pagsasalin ng nakalimbag na mga kagamitan, ay magagamit ng walang bayad. Tumawag sa 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Tigrigna] ተርጎምትን ናይ ዝተፅሓፉ ማተርያላት ትርጉምን ሓዊሱ ናይ ቋንቋ ሓገዝ ግልጋሎት፤ ብዘይ ምንም ክፍሊት ይርከቡ፡፡ ብ 1-800-562-3022 (TRS: 711) ደውሉ፡፡

[Ukrainian] Мовна підтримка, у тому числі послуги перекладачів та переклад друкованих матеріалів, доступна безкоштовно. Зателефонуйте за номером 1-800-562-3022 (TRS: 711).

[Vietnamese] Các dịch vụ trợ giúp ngôn ngữ, bao gồm thông dịch viên và bản dịch tài liệu in, hiện có miễn phí. Gọi 1-800-562-3022 (TRS: 711).

## የርዕስ ማውጫ


እንኳን ወደ Washington Apple Health/Apple Health አገልግሎት በደህና መጡ [4]

የአገልግሎትዎ ካርድ [4]

የመጀመርያ እንክብካቤ [6]

የባህሪይ ጤና በየሀገሩ ዕቅድ [7]

የቀውስ አገልግሎት [9]

የባህሪ ጤና መገናኛ [10]

ለአሜሪካን አላስካና አላስካ ናቲቭ መረጃ [11]

የጤና እርዳታ ለማግኘት ሲፈልጉ የሚችሏቸው አገልግሎቶች [12]

መብትና ሀላፊነትዎ [13]

መገናኛ/ምንጭ [14]


### ይህንን ፅሁፍ የሚቃወም:

ይህ መጽሐፍ እርስዎን ከጥቅማጥቅሞችዎ ጋር የሚያስተዋውቅዎት ሲሆን የእርስዎን መብቶች እና ኃላፊነቶች እንዲሁም እንዴት አገልግሎት ማግኘት እንደምችሉ ያብራራል፡፡ ይህ መጽሐፍ ምን አይነት ሕጋዊ መብቶች ወይም ጥቅምች ያማይ ፈጥር መሆኑን እባክዎን ይገንዘቡ፡፡ ይህ ን አነስተኛ መፅሀፍ እንደ ብቸኛ የ Apple Health (Medicaid) የመረጃ ምንጭ አድርገው በማሰብ መወሰን የለቦትም። ስለ Apple Health የተብራራ መረጃ ለማግኘ ት በ ጤና ጥበቃ ባለስልጣን ድህረ-ገፅ ህጎችና ደምቦች ገፅ **hca.wa.gov/about-hca/rulemaking** ።

# እንኳን ወደ Washington Apple Health በደህና መጡ

*ይህን መፅሓፍ የተሰጡበት ምክንያት በቅርብ ግዜ በዋሽንግተን የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን የሚተዳደረው (HCA) ለ Washington Apple Health (Medicaid) ብቁ ስለሆኑ ነው:: ይህ መፅሃፍ ያለ ማነጅድ ኬር እቅድ እንዴት Apple Health አገልግሎት እንደሚያገኙ መረጃ ይዟል::*




## Apple Health አገልግሎቶች

የ Apple Health ደንበኞች ያለ ማነጅድ ኬር እቅድ ለሚከተሉት አገልግሎቶች ብቁ ናቸው:

- የበሽታ ቅድመ መከላከያና የደህንነት አገልግሎቶች ጨምሮ ከሀኪም ወይም ከሌላ የጤና ባለሙያ ጋር የሚገናኙባቸው ቀጠሮዎች
- የድንገተኛ ህክምና ክትትል
- የወሊድና አዲስ የተወለዱ ህፃናት የጤና ክትትል
- የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎቶች(የጥርስና የአ ይን ደህንነት ክትትል
- የቤተሙከራ አገልግሎቶች
- የሚታዘዙ መድሀኒቶች
- የሆስፒታል ህክምና
- የአጭር ጊዜ ህክምና አገልግሎቶች (አድረው ለማይታከሙ)
- ለመልሶ ማቋቋሚያ እና ማስታገዛ አገልግሎቶች እና ማሳሪያዎች
- የአእምሮ ጤና አገልግሎት
- የአይን መነፅርና ለህፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች (ከ 21 ዓመት በታች ላሉ ህፃናት)
- የረጅም ጊዜ የእርዳታ አገልግሎቶች
- የአእምሮ እድገት ችግር ላለባቸው ግለሰቦች የሚሰጡ አገልግሎቶች
- የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች

** በApple Health የአዋቂዎች መርሀግብር ብቻ ማግኘት ይችላሉ:: የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ 1-800-562-3022 ይደውሉ::*

**ማስታወሻ፡-** ይህ ዝርዝር ለአጠቃላመረጃነት ብቻ የቀረበ እንጂ የApple Health የተጠቀሱትን አገልግሎት ሽፋን ማግኘትን የሚያረጋግጥ አይደለም ። አንድ አንድ የብቁነት መርሀግብሮች፣ ለነዚህ አገልግሎቶች ከገደብ ጋር ብቁ ይሆናሉ:: የ Washington Administrative Code (WAC) ይመልከቱ፡ 182-501-0060.

## የአገልግሎትዎ ካርድ

*የ Apple Health አገልግሎቶች ካርድ በፖስታ ይደርሶታል::*

በ Washington Healthplanfinder አማካኝነት ለ Apple Health ብቁ ከሆኑ ከሁለት ሳምንት በኋላ **wahealthplanfinder.org**፣ ወይ Washington Connection **washingtonconnection.org**፣ በዚህ ምስል እንደሚታየው ሰማያዊ የ Apple Health Services ካርድ (በተጨማሪም ProviderOne ካርድ ተብሎ ይጠራል) ያገኛሉ:: ይህንን ካርድ ይያዙ። ለ Apple Health ሽፋን ብቁ መሆኖትን ያመላክታል::

የአገልግሎቶችዎ ካርድ የሚከተሉትን ያጠቃልላል

- ProviderOne መታወቂያ ቁጥር
- የተሰጠበት ቀን
- ProviderOne ድረ-ገጽ
- የደንበኛ አገልግሎት አድራሻ መረጃ

እርስዎ አዲሱን የአገልግሎት ካርድዎን እንዲሰራ ማድረግ አይጠበቅብዎትም። ካርዱ ን እኛ ከመላካችን በፊት HCA በስራ ላይ መዋል እንዲችል ያደርግሎታል። እያንዳንዱ ሰው በህይወት ዘመኑ አብሮት የሚቆይ የተለየ የProviderOne የደምበኝነት ቁጥር አለው።

## የአገልግሎት ካርዱን ለማግኘት ካልቻሉ ወይም ከጠፋቦት

Apple Health ብቁ ከሆኑ ከሁለት ሳምንት በኋላ የአገልግሎት ካርድ ካልደረሶት፣ እባክዎትን መተኪያ ካርድ ለመጠየቅ Apple Health የደንበኞች አገልግሎትን ያግኙ:: 24/7 በሚከተለው በኦንላይን መግባት ይችላሉ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus** ወይ በስራ ሰዓት በ1-800-562-3022 (ነፃ መስመር) ይደውሉ::

የአገልግሎት ካርዶ ከጠፋቦት፣ ካሉት አማራጮች በመጠቀም በ 24/7 ምትክ መጠየቅ ይችላሉ::

- **በግል ስልክዎ።** ወደ 1-800-562-3022 (ነፃ መስመር) በመደወል ለእራስ አገልግሎት 1 ን ቀጥሎም ለመታወቂያ ካርድ 1ን በመምረጥ ይጠቀሙ።
- **በኮምፒተር በደምበኛ መግቢያ በመጠቀም።** የ Client Portal ን በ **https://www.waproviderone.org/client** ማግኘት ይችላሉ።



በእርስዎ የአገልግሎት ካርድ ላይ “ProviderOne” የሚል ስያሜ ያያሉ። ProviderOne አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መላክ የሚያስችል የ HCA ስርዓት ነው፡፡ በካርዱ ላይ የሰፈረው ቁጥር የProviderOne ደንበኛ ቁጥር ነው።

የጤና ድጋፍ ሰጪዎች ታካሚዎቻቸው በApple Health መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ እንዲረዳቸው ProviderOne ን መጠቀም ይችላሉ። የአድራሻ ለውጥ የመሳሰሉ ለውጦችን በ Washington Healthplanfinder ወይ Washington Connection ሪፖርት ማድረግ እንዳይዘነጉ፡፡

በApple Health ህጋዊ የሆኑ የቤተሰብዎ አባላት በሙሉ የየራሳቸውን የአገልግሎት ካርድ ይቀበላሉ። እያንዳንዱ ሰው በህይወት ዘመኑ አብሮት የሚቆይ የተለየ የ ProviderOne የደምበኝነት ቁጥር አለው።

በቀዳሚ ጊዜያት የApple Health ሽፋን ከነበሮት አዲስ ካርድ አያገኙም። በአገልግሎት ሽፋኑ ላይ ያልተሟላ ቢሆን እንኳን የድሮ ካርድዎት ህጋማዊ ሆኖ ይቀጥላል። የእርስዎ የ ProviderOne የደንበኛ መለያ ቁጥር ተመሳሳይ ሆኖ ይቀጥላል።

ወደ ሀኪም፣ ፋርማሲ ወይ ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ሲሄዱ የአግልግሎት ካርዶን ይውሰዱ፡፡ ፎቶ ያለበት መታወቂያም ሊያስፈልግዎ ይችላል።


# መጀመርያ ደረጃ እንክብካቤ

## የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ የሚያስፈልገው ለምንድነው?

ቀዳሚ የጤና እርዳታ ሰጪው (PCP) የሚጎበኙት ዋናው የጤና ባለሙያ ነው PCP ለእርስዎና ለቤተሰቦ የመጀመርያ እንክብካቤ አገልግሎት ያቀርባል እንዲሁም ከሌሎች አቅራቢዎች ጋር ይቀናጃል፡፡ PCP ስለጤና ታሪኮና አሁን ያሎት የጤና ሁኔታ በማወቅ ጤናዎን ለመከታተል ያስችለዋል፡፡

PCP እንደሚከተለው ዓይነት ሀኪም ሊሆን ይችላል፡

- አድቫንስድ የተመዘገበ ነርስ
- የቤተሰብ ሀኪም
- አቃቤ ሰራይ ሀኪም
- የማዋለድ/የማህፀን ሀኪም
- የህፃናት ሀኪም
- የሀኪም ረዳት



## ቀዳሚ እርዳታ ሰጪዎትን መምረጥ

እርዳታ ሰጪው የማይከብድዎት አይነት ሰው መሆን አለበት። ለ PCP ምን ዓይነት ጾታ እንደሚመርጡ መወሰን ይችላሉ፡፡ ቋንቋውን የሚናገሩ፣ በእርስዎ ጉዳት ሞያ ያላቸው ወይ ባህሎን ሊረዱ የሚችሉ PCP መምረጥ ይችላሉ፡፡

የሚፈልጉት PCP ካሎት፣ መሞከር የሚፈልጉት አቅራቢ ካለ የApple Health fee-for-service የሚቀበሉ መሆናቸውን ይጠይቁ፡፡ ይህን ካደረጉ አቅራቢውን መጠቀም ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡ Apple Health fee-for-service የማይጠቀሙ ከሆነ ሌላ PCP ሊያስፈልጎት ይችላል፡፡ Apple Health የአገልግሎት ካርድ የሚቀበል ማንኛውም አቅራቢ መጠቀም ይችላሉ፡፡

## ለስፔሻሊቲ አገልግሎቶች ሪፈራል ማግኘት

አንድ አንድ ግዜ ለልቦ የልብ ሀኪም ወይ ለህፃናት የጎፃናት ሀኪም ማግኘት ሊያስፈልጎት ይችላል፡፡ PCP ለነዚህ ስፔሻሊቲ አገልግሎቶች ሪፈራል ይሰጦታል፡፡

**ማስታወሻ:** አንድ አንድ ስፔሻሊቲ አገልግሎቶች፣ አገልግሎቱን ከማግኘቶ በፊት ከ HCA ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡ አገልግሎት እንዲያገኙ አቅራቢው በቅድምያ ፈቃድ ይጠይቃል፡፡

## ቀጠሮ እንዴት መያዝ ይቻላል

የጤና እርዳታ ሰጪዎትን ከመረጡ በኋላ ቀጠሮ ለመያዝ ይደውሉ። ለአብዛኞቹ አገልግሎቶች እርዳታ ሰጪውን ለማግኘት ቀጠሮ መያዝ ይኖርብዎታል። አስቸኳይ የጤና ሁኔታ ላ ከሆነ የሚገኙት በትንሽ ቀናት ውስጥ የጤና እርዳታ የሚያደርግሎትን ሰው ማግኘት አለቦት። ምንም እንኳን አጣዳፊ የጤና ሁኔታ ላይ ባይገኙም ለአጠቃላይ ምርመራ ቀጠሮ ይያዙ (የደህንነት መርመራ ይባላል)። አብዛኛውን ጊዜ ለአጠቃላይ ምርመራ ቀጠሮ ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚወስድ አያዘግዩት። ጤና ምርመራ ማግኘት አስፈላጊ ነው ምክንያቱ በሽታው ቀድሞ ከታወቀ ከህመም መከላከል ይችላሉ፡፡

## እርስዎ ክብካቤ ከፈለጉ

ለተከታታይ ወይ ቅድመ እንክብካቤ ለማግኘት PCP ማግኘት ጥሩ ነው፡፡ አስቸኳይ የጤና ችግር ከገጠሞትና ከ PCP ጋር ቀጠሮ መጠበቅ ካልቻሉ እንክብካቤ ለማግኘት ወደ እንክብካቤ ማእከል ይሂዱ በመቀጠል PCP ያግኙ፡፡

ለአደጋ ግዜ እንክብካቤ – ወደ 911 ይደውሉ ወይ ባቅራቢያዎ ወደ እሚገኘው የአደጋ ግዜ እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይሂዱ፡፡ ለምሳሌ ለአደጋ ግዜ፡ የልብ ድካም፣ የተሰበረ አጥንት ወይ አለርጂክ ስሜት፡፡



# የባህሪይ ጤና

የአገልግሎት ካርድ ካሎት የአዕምሮ ጤና እና እጽ በመጠቀም የሚመጡ ችግሮች አገልገሎቶች (በአንድነት የባህሪይ ጤና አገልግሎቶች ተብለው ይጠራሉ) ማግኘት ይችላሉ። በሚከተሉት መንገዶች የባህሪ ጤና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡

- በእንክብካቤ ዕቅድ ቀ?ጥጥር የሚደረግበትን የባሕሪይ ጤና አገልግሎቶችን ብቻ  (BHSO) ያግኙ። ገፅ 9ን ይመልከቱ።
- በ1-800-562-3022 የአፕል ሄልዝ የደንበኛ አገልግሎት ማዕከል ጋር ይደውሉ።

ለውጥ ካደረጉ የባህሪ ጤና ባለሙያ ማሳወቅ እንዳይዘነጉ።

**ያስታውሱ፡** ከእርሶ የጤና እቅድ ጋር የውል ትስስር የሌላው አቅራቢ ጋር ከሄዱ ክፍያ መፈፀም ሊኖረቦት ይችላል።

በ ባህሪያዊ የጤና ክትትል እና በ HCA ፈንድ የሚደረጉ አገልግሎቶች ለማግኘት **hca.wa.gov/mental-health-and-addiction-services** የሚለውን ይጎብኙ።

## ሌሎች መረጃዎች፡

- ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ ልጆችን መጠጥ እና አጸፋሪስ ከመጠቀም ስለመታደግ ምክሮች ለማግኘት**StartTalkingNow.org**።
- ኅረምሶችን ለመርዳት (የኅረምሳ-ምላሽ የእርዳታ መስመር)፡ **866teenlink.org** ወይም 1-866-833-6546.

## የBHO ንጥረ ነገሮችን የመጠቀም ችግር ህክምና የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

**ምርመራ** — ከጤና እርዳታ አስጪው የሚቀርብ ምን አይነት አገልግሎት እንደሚፈልጉ ለማወቅ የሚደረግ ቃለ መጠይቅ።

**አጭር የማሻሻያ የጤና ክትትል** — ለአጭር ጊዜ በሀኪሙ ጣልቃ ገብነት የችግሩን(እፅ ወይም አልኮል) አጠቃቀም ለመቀነስ።

**የማገገሚያ (ከችግሩ መውጫ ክትትል)** — ሙሉ በሙሉ ማቆም እስኪችሉ ድረስ በጊዜ ሂደት የሚወስዱትን የአልኮል ወይም አደንዛዥ እፅ መጠን ለመቀነስ የሚያስችሎት ህክምና። ይህ አገልግሎት በሆስ?ፒታል ሆኖ በታከምን አያካትትም

**በሆስፒታል ውጪ ሆነው እየተመላለሱ የሚደረግ ክትትል** — በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳሉ የግልና የቡድን የምክክር መድረኮች ።

**ጠንከር ያለ ከውጪ እየተመላለሱ የሚታከሙበት** — በዛ ያሉ የግልና የቡድን የምክክር ጊዜያት።

**የአዳሪ ህክምና ክትትል** — የተጣመረ በቀን በክትትል የሚያገኙት የግል ና የቡድን ምክክር እና ትምህርት።

**የማረጋጊያ(የሚያስተኛ መድሀኒት ጥገኝነት ህክምና** — ለውጪ ታካሚዎች ክትትልና እርዳታ። ጥራቱን የጠበቀ ህክምና አና ማማከር አገልግሎት።

**የችግሩ ክትትል** — የህክምና፣ማህበራዊ ፣የትምህርትእና ሌሎች አገልግሎቶች።



## የስነ-ልቦና ጤና አገልግሎቶች፡

**የቅበላ ግምገማ** — ፍላጎትዎችዎንና ግብዎን በመለየት የእርዳታ ሰጪዎት የሚያስፈልጎትን አገልግሎትና ክትትል ያመቻቻል።

**የግል ክትትል አገልግሎቶች** — ከግብዎት እንዲደርሱ የሚያግዙ የምክር እና ሌሎች ተግባሮች።

**የህክምና ክትትል** — መድሀኒት የሚያዝሎትና ስለ ጎንዮሽ ችግሮቹ የሚያስረድዎት ሰራተኞች ያገኛሉ።

**የህክምና ቁጥጥር** — ህክምና ዎት እንዴት እየሄደ እንደሆነና በትክክል እንዲወስዱ የሚረዱዎት ክትትል የሚያደርጉ አገልግሎቶችና።

**የቡድን የህክምና አገልግሎቶች** — ተመሳሳይ ችግር ከገጠማቸው ሰዎች ጋር ተደባልቀው የሚያደርጉት ምክክር።

**የአቻ ድጋፍ** — የአእምሮ ጤና ስርአቱን ለማሰስና እንዲያገግሙ ካገገመ ግለሰቦች የሚሰጦት ድጋፍ።

**አጭር ክትትልና ጣልቃ ገብነት** — በአንድ ችግር ዙሪያ የሚያተኩር አጭር የማማከር አገልግሎት።

**የቤተሰብ ክትትል** — የተሻለ ጠንካራ ግኙኝነትን ከቤተሰብዎ ጋላር በመፍጠር ችግሮችን መቅረፍ።

**ጠንካራ ክትትል** — አላማዎን እንዲያሳኩ የሚረዱዎ አገልግሎቶችን ከ እርዳታ ሰጪው ያገኛሉ።

**የህመም ማስወገጃ ስነ ልቦናዊ ትምህርት** — ድጋፎችንና የድጋፍ አገልግሎቶችን ያካተተ ስለ አእምሮ ህመም፣የአእምሮ ጤና ክትትል እማራጮች ህክምናና ማገገም የ ሚሰጡ ትምህርቶች።

**የቀን ድጋፍ** — ስለ አኗኗር ክህሎቶችየሚያስተምርና የሚደግፍ ሰፊ ፕሮግራም

**የጤና ሁኔታ ምዘናና የህክምና ክትትል ወይም የማህበረሰብ ህክምና** — በህክምና የሚያስፈልግ ለውስጥ ታካሚ የሚደረግ ድጋፍ። ከዚህ አገልግሎት በፊት የውጪ ታካሚ ቅበላ ምዘና አያስፈልጎትም ።

**የማረጋጊያ አገልግሎቶች** — በሆስፒታል እንዳይቆዩ በቤትዎ ወይም ቤትዎን በሚመስል አካባቢ የሚሰጥ አገልግሎት። ከዚህ አገልግሎት በፊት የውስጥ ህክምና ያስፈልጎት እንደሆነ የሚገመግም ምርመራ አያስፈልጎትም ።

**የማገገሚያ ክትትል** — የውስጥና የውጪ ህክምና አገልግሎቶችን ያጣመረ አገልግሎት። ለሚደረግሎት የቅበላ ምዘና ይህ አንዱ አካል ሊሆን ይችላል።

**በመኖሪያ አካባቢ የሚሰጡ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች** — በዛ ያለ ሰው በሚገኝበት ቤት የሚኖሩ ከሆነ የሚሰጥ አገልግሎት።

**የተለየ ምርመራ**— በህፃናት፣በእድሜ ከፍ ባሉ አዋቂዎችና ከተለያየ ባህል በወጡ ግለሰቦች ዙሪያ ልዩ ትምህርት ባለው ባለሙያ እንዲረዱ የሚያደርግ ክትትል።

**ስነ ልቦናዊ ምርመራ**— ለ ዲያግኖሲስ፣ምዘናና ክትትል የሚረዳ ምርምራ።



## የቀውስ አገልግሎት

የቀውስ አገልገሎቶች ቀውስ ላይ ከሆኑ እንዲረጋጉ የሚያስችልዎት እንዲሁም ፍላጎትዎን በይበልጥ ለማሟላት ምቹ በሆነ ቦታ የሚሰጡ የ24 ሰአታት አገልገሎቶች ናቸው፡፡ ለእነዚህ አገልግሎቶች የቅበላ ግምገማ አያስፈልግዎትም፡፡


- ለፈጣን እርዳታ 911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደ ሚገኝ ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል የሂዱ፡፡
- ለአስቸኳይ አህምሮ ጤና ለ988 ይደውሉ፡፡ የቀውስ አገልግሎት ለማግኘትፍቃድ አያስፈልግም፡፡
- የአደጋ ግዜ መስመር ዝርዝር ለማግኘት: **hca.wa.gov/mental-health-crisis-lines** ይጎብኙ፡፡
- የማገገም ድጋፍ መስመር: **waRecoveryHelpLine.org**፡፡ ህክምና ከፈለጉ 24- ሰዓት ነፃ የሚገለገሉባን እና ሚስጢራዊነቱ የተጠቀውን የስልክ መስመር 1-866-789-1511 (TTY 1-206-461-3219). ይጠቀሙ
- ለብሔራዊ የራስ ማጥፋት መከላከያ የሂወት መስመር በ ለ988 ይደውሉ ወይም አጭር መልክት ይላኩለት 1-800-273-8255 (TTY 1-800-799-4889) ይደውሉ፡፡

## የባህሪይ ጤና ድርጅት መገኛዎች

| ድርጅት | ስልክ ቁጥር | የድር ጣቢያ ፡- |
|---|---|---|
| Community Health Plan of Washington (CHPW) | 1-800-440-1561 | **chpw.org** |
| Coordinated Care of Washington (CC) | 1-877-644-4613 | **coordinatedcarehealth.com** |
| Molina Healthcare of Washington (MHW) | 1-800-869-7165 | **molinahealthcare.com** |
| UnitedHealthcare Community Plan (UHC) | 1-877-542-8997 | **uhccommunityplan.com** |
| Wellpoint Washington (WLP)<br>(ቀደም ሲል Amerigroup) | 1-833-731-2167 | **wellpoint.com/wa/medicaid** |

## ማነጅድ ኬር ድርጅት (ለባህርያዊ ጤና አገልግሎት ጥቅም ብቻ)

| County | Community Health Plan of Washington | Coordinated Care | Molina Healthcare of Washington | United Healthcare of Washington | Wellpoint Washington (ቀደም ሲል Amerigroup) |
|---|---|---|---|---|---|
| Adams | X | X | X | | X |
| Asotin | X | X | X | | X |
| Benton | X | X | X | | X |
| Chelan | X | X | X | | X |
| Clallam | X | X | X | X | X |
| Clark | X | X | X | | X |
| Columbia | X | X | X | | X |
| Cowlitz | X | X | X | X | X |
| Douglas | X | X | X | | X |
| Ferry | X | X | X | | X |
| Franklin | X | X | X | | X |
| Garfield | X | X | X | | X |
| Grant | X | X | X | | X |
| Grays Harbor | X | X | X | X | X |
| Island | X | X | X | X | X |
| Jefferson | X | X | X | X | X |
| King | X | X | X | X | X |
| Kitsap | X | X | X | X | X |
| Kittitas | X | X | X | | X |
| Klickitat | X | X | X | | X |
| Lewis | X | X | X | X | X |
| Lincoln | X | X | X | | X |
| Mason | X | X | X | X | X |
| Okanogan | X | X | X | | X |
| Pacific | X | X | X | X | X |
| Pend Oreille | X | X | X | | X |
| Pierce | X | X | X | X | X |
| San Juan | X | X | X | X | X |
| Skagit | X | X | X | X | X |
| Skamania | X | X | X | | X |
| Snohomish | X | X | X | X | X |
| Spokane | X | X | X | | X |
| Stevens | X | X | X | | X |
| Thurston | X | X | X | X | X |
| Wahkiakum | X | X | X | X | X |
| Walla Walla | X | X | X | | X |
| Whatcom | X | X | X | X | X |
| Whitman | X | X | X | | X |
| Yakima | X | X | X | | X |
| የማደጎ እንክብካቤ (በስቴት አቀፍ ደረጃ) | | X | | | |



**Note:** Apple Health ፎስተር ኬር ሀገር አቀፍ ፕሮግራም ሲሆን በዋና መገናኛ (የዋሽንግተን የተባበረ እንክብካቤ)።

## መረጃ ለትውልደ ሕንዲያውያንና አላስካውያን አመርካን

እርሶ ትውልደ ሕንዲያውያን ወይም አላስካውያን አመርካን ከሆኑ፣ እንዴ ሲያትል ሕንዲያን ጤና ቦርድ ወይም የስፖካኔ ኔትቭ ፕሮጀክት በሕንድያን ጤና አገልግሎት ተቋሚ፣ የጎሳ ጤና እንክብካቤ ፕሮግራም ወይም ከተማ ሕንድያ ጤና ፕሮገራም (**UIHP**) በኩል የጤና እንክብካቤ  አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። በእነዚህ  ተቋማት ያሉት አቅራቢዎች ባህሎን፣ ህብረተሰብዎን እና የጤና እንክብካቤ ፍላጎትዎን ያውቃሉ።

የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ ይሰጡዎታል አሊያም በተለየ መስክ ላይ ወደተሻለ ባለሙያ ይልኩዎታል። ማነጅድ ኬር እቅድን (የባሀርያዊ ጤና አገልግሎት እቅድ ብቻ[BHSO])ወይም Apple Health ያለ ማነጅድ ኬር (ይህ Apple Health fee-for-service ተብሎም ይጠራል) ምን ዓይነት ውሳኔ በማድረግ የጤና ሽፋን መምረጥ እነደሚችሉትም ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ስለ ጤና እንክብካቤ ወይም ስለ ጤና እንክብካቤ ሽፋን ጥያቄዎች ካልዎት የጎሳ ወይም UIHP ሰራተኞች ሊያግዙት ይችላሉ፡፡



## የመጀመሪያ እንክብካቤ ጉዳይ አስተዳደር

ከሚተዳደረው እንክብካቤ ዕቅድ ውጪ የአፕልን የጤና ሽፋንን ከመረጡ፣ የተወሰኑ የIHS ተቋማት፣ የጎሳ ጤና እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና የUIHPs የመጀመሪያ እንክብካቤ ጉዳይ አስተዳደርን (PCCM) ያቀርባሉ። PCCM እርስዎን ወዴ እስፔሻልስት ማስተላለፍና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለግምገማና ሕክምና ከእስፔሻልስት ጋር የሕክምናና ጤና መረጃን ማጋራትን ጨምሮ የጤናዎን እንክብካቤ አስተዳደርና ቅንጅትን የሚደግፍ የአፐል የጤና ፕሮግራም ነው። የPCCM ፕሮግራምን የሚፈልጉ ከሆነ ለIHS ተቋምዎን፣ የጎሳ የጤና ፕሮግራምዎን ወይም በPCCM ፕሮግራም የተሳተፉ ከሆነና እርስዎ መመዝገብ የሚችሉ ከሆነ የUIHPን መጠየቅ ይችላሉ። በPCCM ፕሮግራም በማንኛውም ጊዜ መመዝገብ ወይም ከመዝግብ መውጣት ይችላሉ፣ ነገር ግን መመዝግብዎ ወይም ከመዝግብ መውጣትዎ በቀጣይ ሊኖር እስከሚችለው ወር ድረስ ተግባራዊ አይሆንም።.

## የጤና እንክብካቤ የሚገኙበት መንገዶች

HCA ለአሜሪካውያን ህንዶችና አላስካ ትውልዶች ዋሽንግተን ውስጥ ከApple Health ማነጅድ ኬርና Apple Health ሽፋን ያለ ማነጅድ ኬር እንዲመርጡ እድል ይሰጣል፡፡ HCA ይህን የሚያደርገው የህንዲያ ጤና እንክብካቤ አሰጣጥ ስርዓት ችግር ግምት ውስጥ በማስገባትና በባህል ተገቢ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማገዝ የፌደራል ህግ እንዲያከብር ነው፡፡

- ከቀጥጥር ከሚደረገው የጤና እ?ንክብካቤ ዕቅድ ውጪ የሆነ አፐል የሄልዝ ሽፋን ው?ስጥ፣ ማንኛውንም በአፐል ሄልዝ ለአገልግሎት ነፃ ፕሮግራም የሚሳተ?ፈውንና በአሁኑ ጊዜ ታካሚዎችን የሚቀበሉ አቅራቢዎችን መምረጥ ይችላሉ። እነዚህ አቅራቢዎች ፈቃድ የሰ ጣቸውን ሀገረ-ግዛት ሁ?ሉንም መስፈርቶች ማሟልት አለባቸው።አፐል ሄልዝ ለአገልግሎት ነፃ የጤና አቅራቢ ለማግኘት ይጎብኙ **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider**።
- ከApple Health ማነጅድ ኬር ጋር፣ የጤና እንክብካቤዎ በማነጅድ ኬር ደርጅት (MCO) ቁጥጥር ይደረጋሉ፡፡ ይህም ማለት MCO አገልግሎቶችን ለማግኘትና እንክብካቤዎን ለማቀናጀት ለመርዳት እንደ ብቸኛ ማግኛ መንገድ ያገለግላል ማለት ነው።

> *በጎሳ ጤና መርሀግብር ወይም UIHP በመሳሰሉ እንክብካቤዎች ማነጅድ እሚደረጉ ከሆነ ይህ ምርጫ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡*

> *እንክብካቤዎን የሚቆጣጠር ሰው ከሌሎት ይህ ምርጫ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡*

በማንኛውም ጊዜ ምርጫዎ(ዎችዎ) መቀየር ይችላሉ ፣ ይሁን እንጂ ለውጡ እስከሚቀጥለው ወር ተጽዕኖ አይኖረውም፡፡ በIHS አመቻችነት፣ በትራይባል የጤና መርሃግብር ወይም UIHP በኩል ከትራይባል ደጋፊ ጋር ከተሳሰሩ ወይም ትብብር ከፈጠሩ፣ ውሳኔ በመወሰን ላይ ሊያግዝዎት ይችላል፡፡ ማድረግ የፈለጉትን ለውጥና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ጨምሮ ምርጫዎን ለማሳወቅ በተጨማሪም ለጤና እንክብካቤ ባለስልጣን በ1-800-562-3022 የውስጥ መስመር 15480 ማናገር ይችላሉ፡፡

# የጤና እርዳታ ለማግኘት ሊፈልጉ የሚችሏቸው አገልግሎቶች

## እርስዎ አስተርጓሚ ሊፈልጉ ይችላሉ

እንግሊዝኛ የሚመርጡት ቋንቋዎ ካልሆነ ወይም፥ የማይሰሙ የማያዩ፥ ወይም የመስማት ችግር፥ የትርጉም ባለሙያዎች የምልክትን ጨምሮ በተለያዩ ቋንቋዎች ያለምንም ወጪ ይኖራሉ። የጤና እርዳታ ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ ለመዝጋቢው አስተርጓሚ ይፈልጉ እንደሆነ ያሳውቁ። የሚነገረውን ቋንቋ የሚያስተረጉመው አስተርጓሚው ወደ አገልገሎት ሰጪው ቢሮ መሄድ ወይም በእርስዎ ቀጠሮ ወቅት በስልክ አገልግሎት መስጠት ይችላል። የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚው ወደ አገልገሎት ሰጪው ቢሮ መሄድ ወይም በእርስዎ ቀጠሮ ወቅት በቪድዮ አገልግሎት መስጠት ይችላል።

የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ይዘው ከሚመጡ እነዚህን ብቁ አስተርጓሚዎች ቢጠቀሙ ይመረጣል። አስተርጓሚዎቹ የጤና እርዳታ ቃላቶችን የተማሩ ናቸው። እርስዎን ከህክምና ሰጪዎት ጋር ተግባብተው እንዲቀጥሉ ያግዞታል። የበለጠ ለማወቅ **hca.wa.gov/interpreter-services** ይጎብኙ፡፡

## የአካል ጉዳት ካለቦት

የመናገር ፣የመስማት ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ካለቦት ለቀጠሮ በሚመዘገቡበት ወቅት ይናገሩ። መዝጋቢው አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳዎታል።

መስማት የተሳናቸው፣ መስማት የተሳነው፥ መስማት ማየት የተሳነው የተሳናቸው ወይ መስማት የሚቸገሩ ከሆነ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ከፈለጉ እባክዎትን እንግዳ ተቀባዩን አሳውቁ፡፡ ያለ ምንም ክፍያ አስተርጓሚ ባለሙያ ቀርቧል፡፡

## በትራንስፖርት እገዛ ማግኘት ይችላል

ወደቀጠሮዎት ሊሄዱ የሚችሉበት አማራጭ ከሌሎት መጓጓዣ ለማግኘት ይፈድሎታል። ቀጠሮው በ Apple Health አገልግሎት ሽፋን ማግኘት አለበት፡፡ መጓጓዣዎች አውቶቢስ ፣የነዳጅ ዋጋ ቅናሾች፣በጎ ፍቃደኛ ሹፌሮች፣ዊልቼሮች ወይም ሌላ ተሽከርካሪ፣ አውቶብሶችና አውሮፕላንን ሊያካትት ይችላል። የደላሎች ዝርዝር **hca.wa.gov/transportation-help** ላይ ይገኛል፡፡





## *መብትና ሀላፊነትዎ*

*በሕጉ መሰረት ስለሚያገኙት የጤና ክብካቤ አገልግሎት መብት ያለዎት ሲሆን የእርስዎን ጤና ለመጠበቅ እና ለማሻሻል እንዲሁም አላስፈላጊ ወጪዎችን ለማስወገድ የሚረዱዎት የተወሰኑ ግዴታዎች አሉዎት። ቀጠሮዎች ላይ የማይሄዱ ከሆነ፣ከቀዳሚ እርዳታ ሰጪዎ ጋ የማይተባበሩ ከሆነወይም በሌሎች ምክኒያቶች ይህ ሊከሰት ይችላል። ለበለጠ መረጃ እባክዎ ይገናኙን።*



## እነዚህን የማግኘት መብት አሎት፡

- በጤና እርዳታዎት ላይ በሚደረጉ ውሳኔዎች የመተባበር አለመፈለጎትንም በመግለፅ ጭምር።
- ወጪው ምንም ሆነ ምን ስለሁሉም ያሉ የሕክምና አማራጮች ማወቅ።
- ብዙ ሳይጠብቁ አገልግሎቶችን ማግኘት።
- በክብር መስተናገድ። ማግለል በፍፁም አይቻልም። ማንም በዘር ፣ቀለም፣ሀገር፣ፆታ፣የወሲብ ህይወት፣እድሜ፣ሀይማኖት፣ባለው እምነት ወይም አካል ጉዳት ምክኒያት ባልተገባ ወይንም በተለየ መንገድ ሊስተናገድ አይችልም።
- ስለ ጤና እርዳታው የተሰማዎትንእና የሚፈልጉትን በነፃነት የመናገር።
- ግላዊ ጉዳዮን እና መረዳዎን በሚስጥር እንዲጠበቅክዎ ማድረግ።
- የህክምና መዝገቦን ግልባጭ የመጠየቅና የማግኘት።
- አስፈላጊውን የመዝገብ ላይ እርማት የመጠየቅና የማግኘት።
- በሚከተሉትላይ ጥያቄ የማቅረብና መረጃ ማግኘት፡
  - » ስለ ጤና እርዳታዎትና የተሸፈኑ አገልግሎቶች።
  - » ስለ እርዳታ ሰጪዎትና ወደ ሌላ ባለሙያዎችና እርዳታ ሰጪዎች የሚላኩበትን ሂደት የመጠየቅ።
  - » ሁሉንም የእርዳታ አማራጮች የማግኘትና ለምን የተለዩ እርዳታዎችን እንደሚያገኙ።
  - » በብቁነት ውሳኔ ወይ በሽፋን ውሳኔ ካልተስማሙ እንዴት የፍርድ ሂደት ይጠይቃሉ፡፡
- መብትዎ የአእምሮ ጤናና ጎጂ ነገሮችን የመጠቀም አገልግሎቶችን ማግኘትን ያካትታል።
- የአደጋ ስልክ ቁጥር ዝርዝር መቀበል።
- የአእምሮ ወይም የጤና ህክምና ረጂ መግለጫ ቅጾችን የመቀበል።

## የሚከተሉትን የማድረግ ሀላፊነትም አለቦት፡

- በጤና እርዳታዎት ላይ በሚደረጉ ውሳኔዎች የመተባበር አለመፈለጎትንም በመግለፅ ጭምር።
- በቀጠሮ መገኘትና ሰዓት ማክበር። የሚያረፍዱ ከሆነ ወይም ቀጠሮውን የሚሰርዙ ከሆነ ለአገልግሎት ሰጪዎ መ/ቤት ደውለው ያሳውቁ።
- ህክምናውን ለሚሰጥዎት ክፍያን ያገኙ ዘንድ የሚያስፈልገውን መረጃን መስጠት።
- ለአገልግሎት ሰጪዎቹ እርስዎ ከእነሱ የሚፈልጉትን ያህል ክብር ይስጧቸው።
- በሁሉም ቀጠሮዎት ላይ የአገልግሎት ካርዱንና የጤና እቅድ ካርዱን ይዞ መገኘት።
- በሚያስፈልጎት ጊዜ የጤና እርዳታ አገልግሎቶችን ማግኘት።
- የጤና እክሎትን የማወቅና ከስምምነት ላይ በተደረሱ የህክምና አይነቶች ጋ መተባበር።
- የሚያስፈልጎትን የጤና እርዳታ ያገኙ ዘንድ ሙሉ መረጃ ለ ሃኪሞ እና ለጤና እቅድዎ ይስጡ።
- ለጤና እርዳታ ለተስማሙበት ህክምና የሀኪምዎትን ትእዛዝ መከተል።
- የጤና እርዳታ አገልግሎቶችን በአግባቡ መጠቀም። ይህን ካላደረጉ ግን ወደ ታካሚ ምልከታ ወይም Coordination program ሊካተቱ ይችላሉ። በዚህ ፕሮግራም የሚመደብሎት አንድቀዳሚ የጤና እርዳታ ሰጪ ፣አንድ የተወሰኑ መድሀኒቶችን ብቻ የሚያዝሎት ባለሙያ እና አንድ የድንገተኛ ህክምና የማይሰጥ ሆስፒታል ይመደብሎታል።
- የቤተሰብዎት ቁጥር የሚጨምር ከሆነ (እንደ እርግዝና፣ ወሊድና ማደጎ በመውሰድ በመሳሰሉ ምክኒያቶች) ወይንም አንዳንድ ሁኔታዎች ማለትም (የአድራሻ ለውጥ፣ የገቢ መጠን መቀየር ወይም በሜዲኬር ና ከሌሎች ዋስትናዎች ለማግኘት ከበቁ ወዲያውኑ ያሳውቁ)።
- Washington Healthplanfinder ድህረ ገፅ በመጠቀም ሽፋን ለማደስ **wahealthplanfinder.org** ወይ Washington Connection ድህረ ገፅ **washingtonconnection.org** ይጠቀሙ፡፡ የሚቀየሩ ነገሮችንም ለማሳውቅ ይህን ድህረ ገፅ ይጠቀሙ።

## ለጥያቄዎት መልሶችን ከየት ያገኛሉ

| በሚከተሉት ላይ ጥያቄ አልዎትበሚከተሉት አልዎት | ሀብቶች |
|---|---|
| • Washington Apple Health (Medicaid) ሽፋን | ኦንላይን: hca.wa.gov/apple-health |
| • ለጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ስላልዎት ህጋዊነት<br>• የአገልግሎት ካርድ<br>• አገልግሎት አቅራቢን መምረጥ<br>• የተሸፈኑ አገልግሎቶች | Apple Health የደምበኛ አገልግሎት በ1-800-562-3022 በመደወል ከዚያም ለደምበኛ አገልግሎት 3 ትን በመምረጥ ወይም ጥያቄዎትን በ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus** , ወይም ድረገፃችንን ይጠቀሙ: **https://www.waproviderone.org/client** ። . |
| • በምዝገባ መረጃዎት ላይ ማለትም በ አድራሻዎት፣ገቢዎት፣የጋብቻ ሁኔታ፣የእርግዝና፣የወሊድ ወይም በማ ደጎ ልጅ ከወሰዱ ለሚኖሩ ለውጦች። | ለልጆች፣ እርጉዝ ግለሰቦች፣ ላጤ ሰዎች እና ወላች/እንክባቤ ሰጪዎች ሽፋን: **wahealthplanfinder.org** ወይም በ 1-855-923-4633 (TRS: 711) ይደውሉ።<br><br>እድሜየቸው ለገፉ፣ አይነ-ስውራን ወይም አካ ጉዳተኞች ወይም የረዥም-ጊዜ አገልገሎቶች እና ድጋፎች የሚያስፈልጋቸው ሽፋን: **washingtonconnection.org** ወይም በ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ይደውሉ |

## እንዲታወቅ ስለማይፈልጉት የግል ጉዳይ ማስታወሻ

የአገልግሎት ካርድዎ ከስምዎ፣የProviderOne ቁጥርዎ ና ካርዱን ከወሰዱበት ቀን ውጪ ምንም አይነት የግል መረጃዎን አያካትትም። ይህ ካርዱ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ የእርስዎን ሚስጢር እንዲጠበቅ ያደርጋል። የጤና ጥበቃ ባለስልጣን (HCA) ሆነ የጤና እቅድዎ በማንኛውም ጊዜ በቀጥታ እርሶን ለማነጋገር የግል መረጃዎን ለማግኘት እና የአገልግሎት ካርድዎን መተካት አይችልም:: **እንደ ማህበራዊ ዋስትና ቁጥር የመሳሰሉ የግል መረጃዎን ፈጽሞ ለመጠየቅ ስልክ ለሚደውልልዎት ወይም በኢሜይል ለሚጠይቅዎት ግለሰብ አይስጡ።**

የጤና እቅዶችና HCA የጤና መረጃዎን ለርስዎ ጥቅማ ጥቅሞችን ለመስጠት፣ክትትሎችን ፣ክፍያዎችን፣እንዲሁም የጤና እርዳታ ሂደቶችን ለማካሄድ እና በሌሎች ምክንያቶች እንዲገለገሉበት ወይንም ለሌላ አካል እንዲያካፍሉ በህግ ፍቃድም ሆነ ግዴታ አለባቸው። ነገር ግን HCA የጤና መረጃዎን በሚስጥር መያዝ ይጠበቅበታል።

የHCA ን የግል ጉዳዮችአጠባበቅ ስምምነት ለማንበብ **hca.wa.gov** በመግባናት “Privacy” የሚለውን ከታች የሚገኝ ምርጫ ይጫኑ።

Washington State Health Care Authority

P.O. Box 42719
Olympia, WA 98504-2719

HCA 19-065 AM (11/23) Amharic